ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ኢየሱስ ክርስቶስ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

The Conquering Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

**ቍጥር ፱/፳፻፯ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋዲ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የአዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

**በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤**

**አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤**

**በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥ ወንግሥትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤**

**በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥ ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡**

**ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።**

**+ + +**

**የተለያየ ስም በተሰጠው ሃይማኖት እየተጠራችሁ፡ በመላው ዓለም ተሠራጭታችሁ፡ ለምትኖሩ፡ ለወንዶችና ለሴቶች፡ የሰው ወገኖች ኹሉ!**

## አንደኛ

ባለፈው ነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓ. ም. በቍጥር ፩/፳፻፰ በወጣው፡ በመጀመሪያው የዐዋጅ ቃል መሠረት፡ እያንዳንዳችሁ፡ የመልእክቱን ጥሪ ተቀብላችሁ፡ እየራሳችሁን፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ ለዚያ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት አብቅታችሁ የተገኛችሁ፡ ኹላችሁ፡ ዕድለኞች ናችሁ። ይኸውም፡-

በቅድሚያ፡ ጥንቱኑ፡ በየግል አቋማችሁ፡ በዚሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እምነትና ምግባር ጸንታችሁ የምትኖሩ ከኾናችሁ፥ "ፍጹማኑ" ስለኾናችሁ ነው፤

ቀጥሎ፡ አኹን፡ እየራሳችሁን፡ ለዚያ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነት አብቅታችሁ፡ መኖር የጀመራችሁ ከኾናችሁ፥ "ማዕከላውያኑ" ስለኾናችሁ ነው፤

በመጨረሻም፡ ወደፊት፡ እየራሳችሁን፡ ለዚሁ፡ ለፍጹሙ የሕይወት ልዕልና ልታበቁ፡ ቆርጣችሁ ተነሥታችሁ፡ ወደዚሁ ማዕርግ ለመድረስ፡ በገድሉ ጠባብ መንገድ በመጓዝ ላይ ያላችሁ ከኾናችሁ፡ "ወጣንያኑ" ስለኾናችሁ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ ሰው ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም የመጣው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ለሓዋርያው ለቅዱስ ጴጥሮስ እንዳረጋገጠለት ኹሉ፡ እናንተም፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ <u>ወደእግዚአብሔር መንግሥት የገባችሁበትን ቍልፍ፡</u> እነሆ ተቀበላችሁ! የተቀበላችሁትም፡ ከሰው፥ ወይም፡ ከሌላ ፍጡር ሳይኾን፡ እንደጥንቱ ተፈጥሮአችሁ ኹሉ፡ አኹን ደግሞ፡ እንደገና፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ከራሱ፡ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ከእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኑን አውቃችኋል።

እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ እናንተ፡ ኹላችሁ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ፡ ነጋሥያንና ነጋሥያት ልጆችና ካህናት መኾናችሁ ነው፤ ደግሞም፡ በዚያ የዐዋጅ ቃል፡ ራሷን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ለገለጠችው፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡** ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ዜጎቿና ሠራተኞቿ መኾናችሁ ነው።

በዚህም፡ ኹላችሁም፡ እጅግ ደስ ይበላችሁ!

ስለዚህ፡ በየግል ኾነ፥ በኅብረት፡ ሰዎች ባቋቋሟቸው፡ የሃይማኖትና የአገዛዝ፡ የእርሻና የንግድ፥ የትምህርትና የሙያ፥ የሥነ እውቀትና የኪነ ጥበብ፥ የሕግ አውጭነትና ፈጻሚነት፥ ተርጓሚነትና አስከባሪነት፥ የማኅበራዊ ኑሮ ግንባታና እንክብካቤ፥ የተግባረ እድና የማምረቻ፥ የጤና ጥበቃና የሕክምና፥ የምሕንድስናና የሕንፃ፥ የመገናኛና የመጓጓዣ፥ የፀጥታና የሕዝብ ደኅንነት መከላከያ፥ እነዚህንና እነዚህን በመሳሰሉት የሥራ ተቋሞችና የአገልግሎት ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥራችሁና ተመድባችሁ፡ በየሙያችሁና በየችሎታችሁ፥ በባልደረብነትና በባለሥልጣንነት ተሠማርታችሁ፡ በያላችሁበት በምታካኺዱት ተግባራችሁና ግዳጃችሁ፥ ኃላፊነታችሁና ባለአደራነታችሁ፡ ማንን እያገለገላችሁ እንደምትገኙ፡ በእርግጥ አውቃችኋል።

አዎን! እያገለገላችሁ ያላችሁት፡ የፍጡራንና የየራሳችሁ የኾነውንም እንኳ ሳይኾን፡ ሰዎች የከለሏቸው ብሔራውያን አገሮችና ያቋቋሟቸው የአገዛዝ ሥርዓቶች ሳይወስኗት፡ እነርሱን ኹሉ፡ በበላይነት አካትታና አጠቃልላ፡ እየጠበቀችና እየተቈጣጠረች፡ በምድርና በሰማይ፡ በፍጹም ምልዓት ሰፍና፥ መላውን ፍጥረተ ዓለም የምትመራውንና የምታስተዳድረውን፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያን** መኾኑን አውቃችኋል።

በዚህም፡ እንደገና፡ ኹላችሁም፡ እጅግ ደስ ይበላችሁ!

እንግዴህ፡ በእውነትና በመንፈስ በምታበረክቱት፡ በዚህ፡ ነፍሳዊና ሥጋዊ፥ መንፈሳዊና ኹለንተናዊ አገልግሎታችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚመሯችሁና የሚያበረታቷችሁ፥ የሚጠብቋችሁና የሚረዷችሁ፥ የሚመለከቷችሁና የሚቆጣጠሯችሁ፥ ራሳቸው፡ ካህኑ፡ አባት ንጉሣችን ኢየሱስ ክርስቶስና ካህኒቱ እናት ንግሥታችን ድንግል ማርያም፡ መኾናቸውን አውቃችኋል።

እናንተም፡ ኹላችሁ፡ እርስ በርሳችሁ፡ በአካለ ሥጋ መተዋወቅና መነጋገር፥ መገናኘትና መሰባሰብ ሳያስፈልጋችሁ፡ ይህን፡ ነፍሳዊና ሥጋዊ፥ መንፈሳዊና ኹለንተናዊ የኾነ መልካም አገልግሎታችሁን፡ በያላችሁበት፡ በፍጹም ቅንነትና ትጋት፥ ታማኝነትና ንጽሕና፡ ለማነኛውም ፍጡር፡ በእውነትና በመንፈስ ማበርከት እንዳለባችሁ አውቃችኋል።

በዚህ መልክና ይዘት፡ በእውነትና በመንፈስ አምልኮ ኾናችሁ በምታበረክቱት፡ በዚሁ አገልግሎታችሁ ምክንያት፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያን** ሊያጠፋ፡ በታላቅ ብስጭትና ቍጣ ታጥቆ ተነሥቶ ሣለ፡ ነገር ግን፡ ከጥንት ከመሠረት፡ ዐቅዶት የኖረው ዓላማው፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ የተወገደበት፡ ያ ተቃዋሚው የክፋት አበጋዝ፡ የዛሬ ፪ሺ፮ ዓመታት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ብቅዓትና በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ በተገኘው፡ መለኮታዊ ፍትሕ ተበይኖበት፡ ወደጥልቁ ተጥሎ፡ ለሺው ዘመን ከታሠረ በኋላ፡ አኹን፡ የመጨረሻውን ፍርድ ሊቀበል፡ ለጥቂት ጊዜ መፈታቱን አውቃችኋል።

ይኹን እንጂ፡ ወደዘለዓለማዊው ጥፋት እየመራው ያለውን፡ ይህንኑ የክፋት አበጋዝ ለተከተለው፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ወገን፡ ተሠውራ የቆየችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** በታማኞቿና በእውነተኞቿ፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቿ፡ የሃይማኖትና የምግባር ጽናት የተነሣ፡ በቅርቡ፡ በታወጀው የመንፈስ ቅዱስ የአዋጅ ቃል፡ ራሷን መግለጧን አውቃችኋል።

በዚህም ምክንያት፡ እነሆ፡ ይኸው፡ ተቃዋሚዋ የክፋት አበጋዝ፡ የጥፋት ዕቅዱና ዓላማው ከሸፎበት፥ የሥልጣን ቀንዱም ተሠባብሮበትና የተንኰል መረቡ ተበጣጥሶበት፡ ሽንፈቱን አምኖና ተቀብሎ፡ ይኸው፡ ዐፍሮ፡ ወደዐዘቅቱ መመለሱን አውቃችኋል።

አዎን! በዚህም ኹሉ፡ እንደገና፡ እጅግ ደስ ሊላችሁ ይገባል!

## ኹለተኛ

እንግዴህ፡ በዚህ የተልእኳችን ሥርዓት፡ በመደበኛነት የተያያዛችሁትን፡ አገልግሎታችሁን፡ በያላችሁበት በምትቀጥሉበት ጊዜ፡ በአኹኑ ሰዓት፡ ምንነቷንና ማንነቷን በመግለጥ፡ ራሷን፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ በይፋ የከሠተችውን፡ ይህችኑ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** በተጨማሪ፡ በየሙያችሁና በየችሎታችሁ፥ በየዓቅማችሁና በየስጦታችሁም፡ ልታገለግሏት የምትፈልጋችሁና እየጠራቻችሁ ያለች መኾኗን፡ በዚህ፡ በ፪ኛው የአዋጅ ቃል እንድትገነዘቡት ማድረግ አግባብ ኾኗል።

ስለዚህ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ** አካል በኾኑት፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ ውስጥ፡ እየራሳችሁን ደልድላችሁ እያገለገላችሁ ያላችሁ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ኹሉ፡ ቸሩ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ በለገሣችሁ፥ እናንተም፡ በሥልጠና ምርጫችሁ ባገኛችሁት፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ በኾነውና የዘመኑ ሥልጣኔ ባስገኘው ጠቃሚ እውቀታችሁና ሙያችሁ፥ ጥበባችሁና ችሎታችሁ፥ ስጦታችሁና ሀብታችሁ ታገለግሏት ዘንድ፡ እናት አገራችሁና ሃይማኖት መንግሥታችሁ የኾነችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ይኸው፡ ጥሪዋን አቅርባላችኋለች።

እንዲህም ሲባል፡ እዚህ ላይ፡ ኹላችሁም ልትገነዘቡት የሚገባ፡ አንድ ቍም ነገር አለ። ይኸውም፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** እርሷ በሠራችውና የእርሷ በኾነው፡ በሥጋዊውና በነፍሳዊው፥ በመንፈሳዊውና በኹለንተናዊው የፍጥረተ ዓለም አካልና ባሕርይ፡ የጎደላትና የሌላት፥ ያጣችውና የሚያስፈልጋት አንዳች ነገር ኖሮ፡ ያን፡ ለማሟላትና ለመስጠት፥ ለማስገኘትና ለማቅረብ፡ በእኛ በኩል፡ አኹን፡ "ይኼን፥ ይኼን እናድርግላት!" ማለታችን አይደለም። <u>ኹሉ፡ የእርሷ፥ በእርሷና ለእርሷ ነውና።</u>

እኛ፡ ከእርሷ፡ ያለድካምና ያለዋጋ፥ ሳንጠይቅም፡ እንዲያው፡ በከንቱ ያገኘነውን፡ ያንኑ፡ የእርሷ የኾነውን፡ ሃይማኖታዊ ጸጋ፡ እርሷን ደስ ለሚያስሰኛት፡ ለበጎውና ለተቀደሰው፥ ጣፋጭና ፍሬያማ ለኾነው ምግባራዊ በረከት፡ ያለክፍያ በነጻ፡ "መልሰን እናውለው!" ማለታችን መኾኑን፡ ኹላችሁም እንደምትረዱት እናምናለን።

በዚህ ረገድ፡ **ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ልታበረክቱ የምትችሉት አገልግሎት፡ እንደእያንዳንዳችሁ ስጦታና ሙያ ሊኾን ይገባል፤ ይህም፡ ከእግዚአብሔር ያገኛችሁት የተፈጥሮ ጸጋ፡ እውቀት ከኾነ፡ በዚያ እውቀታችሁ፥ የተለየ ሙያ ከኾነ፡ በዚያ ሙያችሁ፥ ጕልበትና ኃይል ከኾነ፥ በዚያ፡ የጕልበት ኃይላችሁ፥ ሥልጣንና ማዕርግ ከኾነ፡ በዚያ ሥልጣናችሁና ማዕርጋችሁ፥ የገንዘብና የንብረት ሀብት ከኾነም፡ በዚያ ገንዘባችሁና ንብረታችሁ፡ "ትሳተፉላችሁ!" ማለት ነው። ይህንም፡ እየራሳችሁ፡ በያላችሁበትና በፈቀዳችሁት መንገድ፡ በተግባር ልታውሉት የሚያስፈልግ ነው።

ከእኛ ጋር በመሳተፍ፡ ልታበረክቱ የምትፈልጉት አገልግሎት ካለ ደግሞ፡ እውቀቱና ሙያው፥ ችሎታውና የገንዘብ ዓቅሙ ያላችሁ ኹሉ፡ ለምሳሌ፡ ከዚህ በሚከተሉት ዘርፎች፡ በያላችሁበት ኹናችሁ፡ ልትፈጽሙት ይቻላችኋል፤ ይኸውም፡-

፩፡ በጎዋ ስሌዳችንና በፌስቡክ መድረካችን፥ በዩቱብ መስኮታችንና በሌሎች የጎዋ ገጾቻችን ላይ በሚወጡ የጽሑፍ፥ የድምፅና የሥዕል መልእክቶቻችን ዝግጅትና አቅርቦት በመካፈል፤፥

፪፡ በግእዝና በኢትዮጵያኛ (ዐማርኛ)፥ እንዲሁም፡ በእንግሊዝኛ የተዘጋጁ መጽሓፎቻችንንና መልእክቶቻችንን፡ ወደየቋንቋው በመተርጐም፤

፫፡ እነዚህን መጽሓፎችና መልእክቶች፥ ሌሎችንም፡ በማኅተም በማራባትና በማሠራጨት፤

፬፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን እውቀትና ልዩ ልዩ ሙያዎች፥ ግእዝንና ቅኔን፥ ዜማንና ቅዱሳት መጻሕፍትን፥ ሥዕልንና እደ ጥበብን፥ የመሳሰሉትን ዕንቍ ቅርሶቻችንን ጠብቆና አሳውቆ ለማስፋፋት፡ በግእዝና በኢትዮጵያኛ፥ እንዲሁም፡ በእንግሊዝኛና በሌሎች ቋንቋዎች በማዘጋጀት፥

፭፡ እነዚህን ሕያዋን መዘክሮችና ውርሶች ለማሳወቅ የሚያስችሉ፡ የሕፃናትና የትልልቆች ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም፤

፮፡ የእነዚህ ቅርሶችና ውርሶች ሕያዋን መዛግብት የኾኑት፡ ምሁራንና ባለሙያዎች፡ የእውቀት ዘራቸውን ዘርተው፡ ለፍሬ ለማብቃት የሚችሉበትን ዕድል አመቻችቶ በማቅረብ፣

፯፡ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖሩ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ወገኖችን ኑሮ ለማሻሻል፡ በተጀመሩ የልማት ዕቅዶች ውስጥ በመሳተፍ ይኾናል።

ይህን ጥሪዋን ሰምታችሁና ተቀብላችሁ፡ "እም የት!" ብላችኋት፡ የእናታችሁን ፈቃድ ለመፈጸም ከተዘጋጃችሁ፡ ልታበረክቱ የምትፈልጉት አገልግሎት፡ ምን ዓይነትና በምንስ መልክ እንደኾነ፡ መልሳችሁን፡ በእነዚሁ የጎዋ ሰሌዳችንና የፌስቡክ መድረካችን አድራሻዎቻችን ልትልኩልን ይቻላል።

**"በኢትዮጵያ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውስጥ፡ በአገልግሎት መካፈል እንፈልጋለን!" በማለት፡ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ፡ ደጋግማችሁ ለጠየቃችሁና በዚሁ ጥያቄያችሁ መሠረት፡ አኹንም እያገለገላችሁ ላላችሁት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ ይህ የአዋጅ ቃልና ጥሪ፡ ምላሽ እንደሚኾናችሁ እናምናለን።

**ተፀውደ፡ በጥቅምት ፫ ቀን፥ ፳፻፮ ዓ. ም. ታወጀ።**

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።